# የሰራተኞች ካሣ ጥቅማ ጥቅሞች እና COVID-19

የሰራተኞች ካሣ ጥቅማ ጥቅሞች ዓላማ፣ እርስዎ ከስራ ነክ ጉዳት ወይም ሕመም ለምሳሌ በስራ ላይ እያሉ በ COVID-19 ከተያዙ በኋላ ለማገገም የሚያስፈልግዎትን የሕክምና ወጪ ለመሸፈን ነው። ከሕመምዎ በሚያገግሙበት ወቅት የሚያጡትን ደመወዝ በከፊል በመተካት ወደ ስራዎ እንዲመለሱ ያግዙዎታል። እነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች የኢሚግሬሽን ሁኔታቸው ምንም ቢሆን ለሰራተኞች የሚቀርቡ ናቸው።

በስራ ገበታዬ ላይ እያለሁ በ COVID-19 ተይዣለሁ ብለው ካመኑ፣ ወዲያውኑ **ለአሰሪዎ በማሳወቅ** የሰራተኞች ካሣ ጥቅማ ጥቅሞች **መጠየቂያን ማቅረብ** አለብዎት።

**ሕመምዎ አጣዳፊ ከሆነ፣ ወደ 911 ይደውሉ** ወይም ወዲያውኑ ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል ይሂዱ። የ COVID-19 ሕመምዎ ከስራ ጋር የተያያዘ መሆኑን ለሕክምና ሰራተኞች ያሳውቁ። ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ማድረግ ከቻሉ፣ ተጨማሪ መመሪያዎችን ለማግኘት **አሰሪዎን ያነጋግሩ** ።

## የክፍያ ጥያቄዎን እንዴት ያቀርባሉ

- የሰራተኞች ካሣ ክፍያ ጥያቄ ለማቅረብ እንደሚፈልጉ ለአሰሪዎ ያሳውቁ ወይም ከሰራተኞች ካሣ መምሪያ ድረ ገጽ የካሣ መጠየቂያ ቅጽን ይሙሉ።
- አሰሪዎ የራሱን ድርሻ በመሙላት ለኢንሹራንሰ ድርጅቱ ይልካል።
- ለመረጃ እንዲሆንዎ አሰሪዎ ኮፒ እንዲሰጥዎ መጠየቅዎን ያረጋግጡ።
- የክፍያ መጠየቂያ ቅጹን ባስገቡ በአንድ ቀን ውስጥ አሰሪዎ ተገቢ የሆነ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ መፍቀድ አለበት። አሰሪዎ እርስዎ ያቀረቡትን የክፍያ ጥያቄ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል በሚወስንበት ወቅት፣ ለሕክምናዎ አገልግሎት እስከ $10,000 ሊያገኙ ይችላሉ።

## በቀጣይ ምን ይከናወናል?

→ ክፍያ ጥያቄዎ ያለበት ሁኔታን በተመለከተ በ14 ቀናት ውስጥ ምላሽ ካላገኙ፣ ለኢንሹራንስ ድርጅቱ ደውለው መረጃ ይጠይቁ።

→ አሰሪዎ በ90 ቀናት ውስጥ የክፍያ ጥያቄዎን ውድቅ ካላደረገ፣ ጉዳትዎ ሽፋን እንደተሰጠው ይቆጠራል።

## አሁንም ጥያቄዎች አሉዎት?

ጥያቄዎች ካሉዎት፣ የሰራተኞች ካሣ መምሪያን ማነጋገር ይችላሉ ወይም በ **1-800-736-7401** በመደወል በድምፅ የተቀዳ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ እዚህ ያግኙ፡
**dir.ca.gov/dwc/injuredworker.htm**

SAFER AT WORK
CALIFORNIA ALL
saferatwork.ca.gov